# ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት

ይህ ክፍለ ሃገር አቀፍ የሆነ ልዩ የጤና አመክሮ በኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና አገልግሎት ማእከል፤ እንግሊዘኛ የመናገር ችሎታ ለሌላቸው ግለሰቦች የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

**ጥ፤ ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎትን ማን ሊጠቀምበት ይችላል?**

ስለአእምሮ በሽታ የግል፤ የቤተሰብ አባል ወይንም ጓድኛ ላይ ስጋት ካለዎት ማእከሉን ያነጋግሩ።

**ጥ፤ ይህ አገልግሎት እኔን እንዴት ሊረዳኝ ይችላል?**

ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት የአእምሮ በሽታን በተመለከተ ስለተጨነቁበት ጉዳይ መግለጫና ምክር በመስጠትና ከሚመለከታቸው አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት እርዳታ ያደርጋል። ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለገዎት፤ የአእመሮ ጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ወይንም ባህልዎንና ቋንቋዎን ከሚያውቅ የአእምሮ ጤና ሠራተኛ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ፤ የአእምሮ ጤና ችግርዎን እንዲቋቋሙ የአጭር ጊዜ እርዳታ ያደርግልዎታል።

የአእምሮ ጤና ሠራተኞች ቀጥለው በተመለከቱት መንገዶች ለረዱዎት ይችላሉ፤

- በሚደረግልዎ ህክምናና የእንክብካቤ ሃሳብ ላይ እርዳታ ማድረግ፡
- የአእምሮ ጤናዎን በተመለከተ፤ በሚናገሩት ቋንቋ ምክክር ለማድረግ መገናኘትና፤
- የአእምሮ ጤናዎን ጉዳይ ለቤተሰብ አባላትዎ ማስረዳት፤
- ከአእምሮ በሽታ ችግርዎ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የአጭር ጊዜ ድጋፍ ወይንም አመክሮ መስጠት ናቸው።

**ጥ፤ ከዚህ የተለየ ምን እርዳታ ታደርጋላችሁ?**

ማእከሉ የአእምሮ በሽታና ተመሳሳይ ችግሮችን በተመለከተ ብዙ የጽሑፍ መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎቸ አዘጋጅቷል። ስለምልክቶቹ፤ ስለህክምናው፤ ስለመድሃኒቱና በአካባቢው ስለሚገኙት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችና ስለመሳሰሉት ለመወያየት ከፈለጉ፤ ለማእከሉ መደወል ይችላሉ።

**ጥ፤ አገለግሎቱ ምስጢር ይጠብቃል?**

አዎን፤ የአእምሮ ጤና ሠራተኞቻችን፤ እንደሌሎቹ የጤና አገልግሎቶች ሁሉ፤ ጥብቅ በሆነ ምስጢር የመጠበቅ የስርአት ግዴታ አለባቸው። ስለሆነም፤ ያለፈቃድዎ ስለጉዳይዎ ከማንም ጋር መወያየት አይችሉም።

**ጥ፤ ከሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አግልግሎት ምን አይነት አገልግሎት አገኛለሁ ብዬ እጠብቃለሁ?**

በክብር፤ ብኩራትና ግለኝነትዎን ከቁጥር በማስገባት፤ እንዲሁም ሃይማኖትዎንና ባህልዎን በማገናዘብ ህክምና እንዲደርግልዎት መጠበቅ ይችላሉ።

ከአእምሮ ጤና ሠራተኞችም ሆነ ባህልዎን ወይንም ቋንቋዎን ከሚያውቅ ሰው ጋር ከመገናኘትዎ በፊት ፈቃድዎን በጽሑፍ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።

**ጥ፤ ከመሥሪያ ቤቱ ጋር እንዴት መገናኘት እችላለሁ?**

ብሪዝበን ከተማ ከሆኑ፤ በስልክ ቁጥር (07) 3240-2833 ወይንም ከብሪዝበን ከተማ ውጪ ከሆኑ 1800 188 189 መደወል ይችላሉ። ከሰኞ እስከ አርብ 8:30 ጠዋት ጀምሮ እስከ 4:30 ከሰአት በኋላ ደውለው የህክምና አገልግሎት አስተባባሪውን ማነጋገር ይችላሉ።

**ጥ፤ እንግሊዘኛ መናገር አልችልም፤ እንዴት አድርጌ ለመሥሪያ ቤቱ መደወል እችላለሁ?**

የትርጉም አገልግሎትን በ131450 ደውለው ቋንቋዎን የሚናገር አስተርጓሚ በመጠየቅ፤ ከኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል ጋር በ (07) 3240-2833 ደውለው እንዲያገናኙዎት መጠየቅ ይችላሉ። የሶስት በኩል የስልክ ግንኙነት ሊካሄድ ይችላል።

**የኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል**
175 ሜልበርን ጎዳና፤ ደቡብ ብሪዝበን (South Brisbane)
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 5767፤ በምእራብ አኳያ (West End)
Q 4101

ስልክ፤ (07) 3240-2833
ፋክስ፤ (07) 3240 2282
በነፃ ጥሪ፤ 1800 188 189
(ከብሪዝበን ከተማ ውጭ)
ኢሜል፤ tccs@health.qld.gov.au

የሥራ ሰአት፤ ከሰኞ-እስከ አርብ
8:30 ጠዋት - 5:00 ከሰአት በኋላ

Queensland Government
Queensland Health

AMHARIC